# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

፰




ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ.ም.

## ለውይይት መነሻ

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፩ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው ።

# የታሪክ ቁስ አካልነት

( ካለፈው የቀጠለ )

፩ኛ ትምህርት—ከን- ዓ-

፪ኛ/ የማርክስ ፍልስፍና ኅብረተሰብን ዲያሌክቲካዊ በሆነ መንገድ ይመለከታል ። ይህ ማለት በኅብረተሰብ ውስጥ የሚደረጉትን ለውጦች ሲያጠና በአራቱ የዲያሌክቲክስ አጠቃላይ የለውጥ ሕጎች እየተጠቀመ ነው ማለት ነው ። እነዚህን ሕግጋት ዲያሌክቲካዊ ቁስ አካልነትን ስናጠና አይተናቸዋል ። የሚቀረን በኅብረተሰብ ላይ እነዚህ ሕጎች እንዴት ከሥራ ላይ እንደሚውሉ መመልከት ነው ።

በዲያሌክቲክስ የምርምር ስልት መሠረት ታሪክ የተዘበራረቁ የአጋጣሚ ድርጊቶች ጥርቅም ሳይሆን የተስተካከለና የተቀነባበረ የዲያሌክቲክስን ጠቅላላ የለውጥ ሕጎች የሚከተል የወደፊት ርምጃ ነው ማለት ነው ።

የታሪክ የለውጥ ሕጎችም እንደማንኛውም የሳይንስ ሕጎች በነባራዊ ሁኔታ ያሉትና ከሥራ ላይ የሚውሉ ሕጎች ናቸው ። እነዚህ ሕጎች በቅድሚያ ሊታወቁ ይችላሉ ። ከሥራም ላይ ሰው ሊያውላቸው ይችላል ። ሰዎች እነዚህን ሕጎች ሊሽሯቸው አይችሉም ። ወይም ደግሞ ሌሎች አዳዲስ ሕጎች ሊያወጡ አይችሉም ። ነገር ግን ያሉትን ሕጎች በማወቅ ሊጠቀሙባቸውና ከታሪክ ጋር አብረው ለመራመድ ሆን ብለው ሊታገሉ ይችላሉ ። እነዚህ ሕግጋት የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ በዲያሌክቲክስ የጥናት ስልት መሠረት ማንኛውም ነገር የተያያዘና በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ነው ። ኅብረተሰብም እንዲሁ ነው ። ከእንቅስቃሴ በስተቀር ዘለዓለማዊ የሚባል ነገር የለም በኅብረተሰብ ውስጥ ዘመን ዘመንን ይተካል ። የሰው አስተሳሰብ ይለወጣል ። አዲሱ አሮጌውን ይሽራል ። ሞት ሕይወትን ይሽራል ። ለምሳሌ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፪ « የዘውዱ አወራረስ ከኃይለ ሥላሴ ዘር ሳይወጣ ለዘለዓለም ይኖራል» ይል ነበር። ዘለዓለማዊ የሚባል ነገር የለም ከሚለው የዲያሌክቲክስ ሕግ አንጻር ይህ አነጋገር ፀረ—ሳይንስ አነጋገር መሆኑ ግልጽ ነው ። ተራማጅ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ደግሞ እንኳን ዘውዱ ይቅርና ራሱ የዘውዱ መሠረት የፊውዳል ሥርዓት መፍረስ እንዳለበትና እንደሚፈርስ በመገንዘብ ፊውዳሊዝም ይውደም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል ብለው ይታገሉ ነበር ። በዚሁ አንጻር ፀረ—ሳይንስ በሆነ የምርምር ስልት የሚያጠኑ ሰዎች ኅብረተሰብን ሲያጠኑ አመጣጡና ሂደቱ ላይ አያተኩሩም ። ለምሳሌ ድኅነትን ብቻ ለማጥፋት ሲልፈጉ ድኃ ማለት ቡትቶ የሚለብስና የሚበላው የሚቸግረው ነው ከሚለው ይነሣሉ ። ወደኋላ ቢመለከቱ ደኃ ምንጊዜም ነበር ለማለት ነው ። ወደፊት ቢያተኩሩ ደኃ ምንጊዜም ይኖራል ለማለት ነው ። በዲያሌክቲክስ የምርምር ስልት የሚጠቀም ሰው ግን ማንኛውንም ኅብረተሰብና ኅብረተሰብ ነክ ጉዳይ ሲያጠና ከየት መጣ ? ምንድን ነው ? መጥፋቱ ስለማይቀር ደግሞ የሚተካውስ ነገር ምንድን ነው ? ብሎ ይመራመራል ። ስለሆነም በዲያሌክቲክስ የምርምር ስልት የሚጠቀም ሰው ሁሉን ነገር ሲያጠና አተኩሮ የሚመለከተው እንቅስቃሴውን ነው ። ኅብረተሰብንም እንደዚሁ ።

በሌላ በኩል ደግሞ የዲያሌክቲክስ የለውጥ ሕግ ሁሉ ነገር በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ላይ ነው ብሎ ሁሉ ነገር በዓለም ላይ ፤ ዓለም ራሷ ብትሆን ጠቅላላው ዩኒቨርስ የተያያዘና የተቀነባበረ እንደሆነ ያስተምረናል ። ምንም ነገር ብቻውን ተነጥሎ የቆመ የለም ። ከሌሎች ነገሮች ጋር የተያያዘና የሌሎች ነገሮች ሁሉ ተጽዕኖ ያለበት ነው ። እሱም ደግሞ መልሶ በአካባቢው ላይ ተጽዕኖ አለው ።

ስለሆነም በኅብረተሰብም ውስጥ ማንኛውንም ነገር ስናጠና ከአካባቢው ጋር አዛምደን ካልተመለከትነው ምንነቱን በሚገባ ልንረዳ አንችልም ። ከአካባቢው ነጥለን ካየነው ምንም ነገር ጥሩም ነው መጥፎም ነው ብለን በደፈናው መናገር አንችልም ።

ለምሳሌ ካፒታሊዝምን እንውሰድ ። ይህ ሥርዓት በአሁኑ ጊዜ የሚኮነንና አድኃሪ ሥርዓት ነው ነገር ግን የሚኮነንና አድኃሪ የሚሆነው በዛሬው የዓለም ሁኔታና የሰው ልጆች እድገት ደረጃ ጋር እየተዛመደ ሲጠና ነው ። የፊውዳል ሥርዓትን አፈራርሶ በተነሣበትና ገና ታዳጊ በነበረበት ዘመን አካባቢ ካፒታሊዝም ተራማጅ ሥርዓት ነበር ። ነገር ግን በዚያ በተወለደበት ዘመንና አካባቢ ተራማጅ ነበር ተብሎ አሁንም ተራማጅ ነው ማለት አይቻልም ። ምክንያቱም ዛሬ ወቅቱ ፈጽሞ የተለየ ወቅት ስለሆነ ነው ።

ሁሉ ነገር የተያያዘ ነው የሚለው የዲያሌክቲክስ ሕግ በመኖሩ የተነሣ በማርክሲዝም አስተሳሰብ አንድ ነገር ስናጠና የግድ ከአካባቢውና ከጊዜው ሁኔታ ጋር አዛምደን መመልከት እንዳለብን ይነግረናል ። ይህንን ማድረግ ካልቻልንና የኅብረተሰቡን ችግሮች ከአካባቢያቸው እየነጠልን ከተመለከትናቸው ትክክለኛ የትግል ስልት እያወጣን አብዮታዊ ትግሉን ማካሔድ አንችልም ።

ለ/ ማንኛውንም ነገር የሚያንቀሳቅሰው በውስጡ የያዛቸው የተቃራኒ ነገሮች ውህደትና ትግል ነው ። ሕይወት የሚሰጠው ፤ የሚያኖረው ፤ በኋላም የሚያጠፋውና በሌላ በአዲስ ነገር የሚተካው በውስጡ አቅፎ የያዛቸው ተቃራኒ ነገሮች በመካከላቸው የማያቋርጥ ትግል ስለሚያደርጉ ነው ።

ይህንን በኅብረተሰብ አንጻር ለማየት ለምሳሌ ፊውዳሊዝምን እንውሰድ ። በዚህ ሥርዓት ውስጥ ባለርስት ብቻውን አይደለም ። ተቃራኒው ጭሰኛም አብሮት ከሌለ ባለርስቱ ሊኖር አይችልም ። ካፒታሊስት ሥርዓት ደግሞ ከበርቴንና ወዝ አደርን አጣምሮ የያዘ ሥርዓት ነው ። ከበርቴ ያለወዝ አደር ሊኖር አይችልም ። በጠቅላላው አይዲያሊስት (ሕሊናውያን ) ፈላስፎች ሀብታምን ከድኃ ፤ በዝባዥን ከተበዝባዥ እየለየ ሁለት ፈጽሞ ግንኙነት የሌላቸው ነገሮች ሊያደርጓቸው ይሞክራሉ ። እነማርክስ ግን አንደኛው ያለ ሌላው ሊኖሩ የማይችሉ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ ።

የገጠርን መሬት የመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በማድረግ የመሳፍንቱን ሥርዓት ለመደምሰስ የሚያስችል አዋጅ በወጣ ጊዜ በመላ አገሪቱ ውስጥ ብዙ ሕዝብ ወጥቶ ሰላማዊ ሠልፍ ማድረጉ ትዝ ይለናል ። የዚያን ዕለት « ዋይ ዋይ ባላባት ዋይ ዋይ መሳፍንት » የሚሉትን መዝሙሮች ሁላችን ሰምተናል ። ግን የዚያን ዕለት ሞተ የሚባለው ባለርስት ብቻ ነበር ወይ ? አይደለም ። በዚያው ልክ ፤ከዚያው ጋር ተያይዞ የዚያን ዕለት መሞት የጀመረው ጪሰኝነትም ነው ።

ነገር ግን ፊውዳሊዝም እንዲጠፋ ከተፈለገ ባለርስትነትም ጪሰኝነትም መጥፋት አለባቸው ስለተባለው ጠቅላላ እልቂት ይሆናል ማለት አይደለም ። ከስድስት ዓመታት በፊት « ታጠቅ» በተባለው የአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር መጽሔት ላይ ተጽፎ የሚከተለውን እናገኛለን ።

« የነፃነት ትግል ረጅም ፤ አታካችና መራራ ትግል ነው ። ሥርዓተ ማኅበራችን ድብልቅልቋ ወጥቶና ትንንቁ ተፈጽሞ የሕዝባችን የነፃነት ትግል ከታሰበው ግብ ሲደርስ ማንም ሰው እንደቀድሞው አይሆንም ። ብዙ መሠረታዊ ለውጦች ይኖራሉ ። አውሎ ንፋሱ ባለፈበት ሁሉ በግለሰቡ ፤ በቤተሰቡ በኅብረተሰቡ በጠቅላላው በሀገሪቷ የቀድሞ የገዥና የተገዥ መንፈስ በሙሉ ተጠራርጎ ተጥሎ የአዲስ ኢትዮጵያና የአዲስ ኢትዮጵያዊ ጽኑ መሠረት በያለበት ሥር ሰዶ እናገኘዋለን ። መራራው ትግል አልፎ ፀሐይቱ የቀድሞዋ ፀሐይ አይደለችም ። ያኔ ለሁሉም ታበራለች ። የቀድሞ ኢትዮጵያውያን ገዥም ሆኑ ተገዥ በአንድነት ድምጥማጣቸው ጠፍቷል ከእንግዲህ አዲስ ሰው አዲስ ኢትዮጵያዊ ነው ። »

እንደማንኛውም ነገር ኅብረተሰብንም የሚያራምደው የተቃራኒዎች ትግል ነው ። እነማርክስ ኅብረተሰቦች በመደብ ከተከፋፈሉበት ጊዜ ጀምሮም ይህ ሀቅ እንዳለ ሲያመለክቱ « እስከዛሬ ያለው የሰው ዘር ታሪክ ( ከጋርዮሽ ዘመን በስተቀር ) የመደቦች ትግል ታሪክ ነው » ብለዋል ። ይህንን ከተረዳን ሁለት መሠረታዊ ሀቆችን እንገነዘባለን ።

አንደኛ ጭቆና የሚጠፋው እውስጡ አቀራኝቶና

እያታገለ በያዛቸው ተቃራኒ ነገሮች በጨቋኝና በተጨቋኝ ትግል ነው ። የኢትዮጵያ ፊውዳል ሥርዓትም የሚጠፋው በባለርስትና በጢሰኛ መካከል በሚደረገው ትግል ነው ። ይህም ማለት ዛሬ በሀገራችን በመገርሰስ ላይ ያለውን ፊውዳል ሥርዓት ሊያጠፋው የሚችለው የአርሶ አደሩ የተደራጀ ትግል ነው ማለት ነው ። ለአርሶ አደሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቂት ግንባር ቀደሞች ብቻቸውን ፊውዳሊዝምን « ደምስሰውለት » አዲስ ሥርዓት በወርቅ ሳህን አርገው ያቀርቡለታል ማለት ከማርክስ ፍልስፍና የራቀ አስተሳሰብ ነው ማለት ነው ። ሁለተኛ ፀረ— ሳይንስ የሆነ የምርምር ስልት ያላቸው ሰዎች የመደቦች ትግል ጊዜ ማጥፋት ይመስላቸዋል ።

ነገር ግን የጭቆና አገዛዝ ከሀገራችን እንዲወገድ የሚፈልግ አብዮታዊ ለውጥ የሚመጣው ከመደቦች ትግል መግፋት መሆኑን መገንዘብና ይልቁንስ የነፃነታችንን ቀን ማራዘምና ጊዜን ማጥፋት የመደቦች ትግልን ማቀዝቀዝ እንደሆነ መገንዘብ አለበት ስለሆነም የመደቦችን ትግል ማፋፋም እንጂ ማቀዝቀዝ የለበትም ። የነፃነት ትግሉ እንደሆነ አንዱ መደብ ሌላውን ሳያጠፋው የሚቆም ነገር አይደለም ። ስለዚህ ከመሀል ቆሞ አስታራቂነት አይቻልም ። ማደናቀፍ ይሆናል ።

« የነፃነት ትግል የኳስ ጨዋታ አይደለም ። ዳኛም ተመልካችም የለውም ። በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለ አንዳንድ ግለሰብ ከዚህ ወይም ከዚያ አንዱን ወገን የግድ መርጦ በሙሉ ኃይሉና በሙሉ ልቡ መሳተፍ ይኖርበታል ። » ( ታጠቅ ሰኔ ፲፱፻፷፪ )

ትግሉን ማፋፋሙን ትቶ መሀል ገብቼ እገለግላለሁ የሚል ሁሉ ታዳጊው እንዲያድግ ፤ አዲሱ አሮጌውን እንዳይተካ የሚያደናቅፍ አድኃሪ ነው ማለት ነው ።

ይህም ስለተባለ ደግሞ ማፋፋም የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙን ማግኘት አለበት ። «የዕብድ ገላጋይ ሾተል ያቀብላል » ዓይነቱ መሆን የለበትም ። ትግሉ የሚደረገው ከዚህ የተፋፋመ ትግል ኅብረተሰባችን መልክ ይዞ ፤ በአዲስ መሠረት ላይ ተጠናክሮ እንዲወጣ ለማድረግ ነው ። ስለዚህ ማፋፋም ማለት ትግሉን ማደራጀት ፤ ሰፊው ሕዝብ የመደብ ጠላቱን ለይቶ እንዲያውቅ ጠላቱን እየደመሰሰ አዲስ ሥርዓት እንዲገነባ ከሱው ጋር በግንባር ቀደምነት ተዋሕዶና አንድ ዓላማ ባለው ስልት ትግሉን መምራት ማለት ነው ።

ሐ. ማንኛውም ነገር በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ከብዛት ወደ ዓይነት መለወጥ የሚለውን የዲያሌክቲክስ የለውጥ ሕግ ይከተላል ። በተቃራኒዎች ትግል ቀስ በቀስ የሚጠራቀመው ለውጥ አንድ የተወሰነ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ ማንኛውንም ነገር መሠረታዊ መልኩንና ጠባዩን ከመ ቅጽበት ይለውጣል ።

ለዚህ መቼስ ባለፈው እትም የጠቀስነውን የውሀ ምሳሌ ማስታወስ ይበቃል ። በኅብረተሰቦችም ውስጥ የሚደረገው መለዋወጥ በዚህ ዓይን ሊታይ ይቻላል ። በኅብረተሰቡ ውስጥ ባሉት ቅራኔዎች የተነሣ በበዝባዥና በተበዝባዥ መሀከል የሚደረገው ትግል እየተፋፋመ ይሄዳል ትግሉ እየተሟሟቀና እየተጠራቀመ ይሄድና አንድ የተወሰነ ደረጃ ላይ ሲደርስ ቅራኔ ውን ጨርሶ የሚፈታ መሠረታዊ ለውጥ ወይም አብዮት ይደረጋል አብዮት ማለት ትግሉ ተፋፍሞ ከፍተኛ ደረጃ ሲደርስ የሚከናወን የኅብረተሰብ ሹም ሽር ነው ። ገዥ መደብ የነበረው ተገዥ ይሆናል ። ተገዥ የነበረው ገዥ ይሆናል ። ከዚህ እንግዲህ ሁለት መሠረታዊ ሀቆችን እናገኛለን ።

አንደኛ ሳይሞቅ የሚፈላ ውሀ የለም ። በኅብረተሰብ ውስጥ መስዋዕትነትና ትግል ሳይደረግበትና ሳይጠራቀምበት በድንገት ከሰማይ ዱብ የሚል መሠረታዊ ለውጥ የለም ። ዛሬ በሀገራችን የሚታየው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ድንገት ከሰማይ ዱብ ያለባቸውና እንዲሁ በድንገት አንዳንድ « ክፉ ሰዎች ጠንስሰው ያመጡት ወይም ደግሞ« እግዜር » ከኢትዮጵያ ፊቱን በድንገት ስላዞረባት «ከላይ የወረደ ቁጣ» የሚያደርጉት ሰዎች አሉ ። እርግጥ ነው ለነዚህ ሰዎች በተለይ ደግሞ በገዥው መደብ አስተሳሰብ ለተበከሉትም እንደ መሳፍንቱ ሥርዓታችን «እዘለዓለም ይቆያል» ይሉ ለነበሩት ለውጡ ሲጠራቀም ፈጽሞ አልታያቸውም ነበር ።

ተራማጁስ ወገን? ተራማጆች ከነሱም ውስጥ በተለይ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አብዮት እንደሚመጣ ፤ ይህ ሥርዓት እንደሚፈርስ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ይህም እንዲሆን በታላቅ ጀግንነት ይታገሉ ነበር ። ይህ ሥርዓት እንዲፈርስ በሚታገሉና «ዘለዓለማዊ» መስሎ በሚታያቸው መሀከል ስለነበረው የርእዮተ ዓለም ትግል ከአምስት ዓመታት በፊት የአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአንደኛ መግለጫው የሚከተለውን ጽፎ ነበር ።




«አንዳንዶች የመደብ ትግል ለጊዜው በግልጽ አይታያቸውም ። ተወልደው ያደጉበት የፊውዳል መደብ ሕሊናቸውን ሸፍኖታል ።የኢምፔሪያሊስቶች የባህል ወረራ ራሳቸውን አስቷቸዋል ። አስተሳሰባቸውን አቃውሶታል ። ስለዚህ በአካባቢያቸው የሚደረገው ትግል ፤ በሀገራችን ሰማይ ላይ የሚያንዣብበው የትግል ማዕበል ፈጽሞ አይታያቸውም ። በቁማቸው ተኝተዋል ። እኛ ዛሬ ስለተያዘው ትግል ስንወያይ ወደፊትም የሕዝብ ትግል እየተፋፋመ ሄዶ በዝባዦች እንደሚደመሰሱ ያለንን የጠበቀ እምነት ስንገልጽ እህል ውሀ ሆኖ ያሳደጋቸው የሕዝብ ንቀትና እብሪት ፤ ሥርዓታችን ለዘለዓለም ይቆያል በሚል እምነት ታግዞ እምነታችንን የልጅ ጨዋታ ያደረጉታል ። »

ግን የልጅ ጨዋታ አልነበረም ። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አብዮታዊ መልኩን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ በዚህ እምነት በመገፋፋት «የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል » እያለ ከአድኃሪ ኃይሎች ጋር የተጋፈጠው እንግዲህ ይህ ሀቅ በድንገት ታግሎለት ወይም ደግሞ «ጠንቋይ ቀልቦ » ደርሶበት አልነበረም ። ከላይ የጠቀስነው መግለጫ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ሲጽፍ ።

«ንቅናቄያችን አድጎ ከዚህ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው በአካባቢው በሚካሄደው ሕዝባዊ ትግል በመታገዙና የታሪክንም እርምጃ ሕጎች ተረድቶ የመደቦች ትግልን መሠረታዊ ሃሳብ በመቀበሉ የታሪክም አራማጅ ኃይል ይኸው የመደቦች ትግል መሆኑን በማጤኑና በሀገራችንም እየተፋፋመ የሚሄደውን ትግል መደባዊ መልክ አበጥሮ በመገንዘቡ ነው ። » ብሎ ነበር ።

ሳይሞቅ የሚፈላ ውሀ የለም አልን ። ያለ ትግል ያለመስዋዕትነት የሚደረግ አብዮት የለም አልን ። ከዚህስ ሌላ ምን ሁለተኛ ሀቅ አለ? ሞቆ መፍላቱም የማይቀር መሆኑ ነው ። ሁለተኛው ሀቅ የአንድ ሕዝብ መስዋዕትነትና ትግልም ይዘገያል እንጂ ሙሉ በሙሉ ማሸነፍና ትናንሿ ትግል ተጠራቅማ ጠቅላላ የኅብረተሰብ ሹም ሽር ወይም አብዮት ማምጣቷ የማይቀር ነው ። በዚህ አስተሳሰብ ከሄድን ደግሞ ሪፎርም ወይም የጥገና ለውጥ የሚባለው ነገር እርግጥ የትግል ደረጃ ውጤት ቢሆንም፤አንድ ሕዝብ በዚህ ብቻ ቀስ በቀስ «እየተሻሻለ » አይቀጥልም ። የወደቀው ሥርዓት የሕዝብ ትግል ባስጨነቀው ቍጥር ጥቃቅንና በዚያው በገዥ መደብ ውስጥ ጥቃቅን ሹም ሽር እያደረገ ጠቅላላውን የኅብረተሰብ ሹም ሽር ለማስቀረት ይታገል እንደነበረ እናውቃለን ። ይህ ግን ውሀ ሞቆ መፍላቱ እንደማይቀር ትግል ተጠራቅሞ አብዮት እንደማይቀር የአድኃሪው መንግሥት ሹም ሽር በምንም ዓይነት አብዮትን እንደማያስቀር ለማስረዳትና አስፈላጊው ጠቅላላ የኅብረተሰቡ ሹም ሽር እንደሆነ ለማሳየት «ትግላችን» በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር መጽሔት ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. የሚከተለውን ጽፎ ነበር።

«ሹም ሽር ብሎ ፊሊጥ ለውጥ ማስታገሻ ፤
የግብዝ ሽልማት የግብዞች ጉርሻ ።
ጣራ ማሳመር ነው ቤት እየፈረሰ ፤
የሹም ሽር መሻሪያው ጊዜው ከደረሰ» ።
በቃ ሹም ሽር ይቅር ከቤተ መንግሥቱ ፤
ሀብታም ብቻ ይሻር ይሰበር ጉልበቱ ፤
ድኃ መርጦ ይሹም የሱነው ሰዓቱ ።

ባጭሩ የዲያሌክቲክስ አጠቃላይ የለውጥ ሕግ አብዮት ጊዜውን ጠብቆ የሚመጣ ጊዜውን ጠብቆ የማይቀር የተፈጥሮ ሕግ እንጂ «ክፉ» ወይም «ደግ» አጋጣሚ ተብሎ ሊገመት እንደማይቻል ያስረዳናል ። ስለዚህ አብዮታዊ ነኝ የሚል ሁሉ አብዮት እንደማይቀር ፤ በጥቃቅን ለውጦች ብቻ «ዘለዓለም» መቀጠል እንደማይችል ተገንዝቦ በዚህም አቅጣጫ ለኅብረተሰቡ ሹም ሽር መታገል አለበት ማለት ነው ።

መ. የሻሪ ሽረት ሕግና የኅብረተሰቦች ዕድገት

በዲያሌክቲክስ የለውጥ ሕግ መሠረት የማንኛውም ነገር እንቅስቃሴ የሚከተለው አቅጣጫ ከቀላሉ ወደተወሳሰበው ፤ ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ ፤ ወደኋላ ከቀረው ወደፊት የተራመደ ነው ። በኅብረተሰቦች አንፃር ይህንን በምንመለከትበት ጊዜ የታሪክ ሂደት አጠቃላይ አቅጣጫ ወደፊት እንደሆነ እንገነዘባለን ።

ማንኛውም ኅብረተሰብ በማያቋርጥና ዘለዓለማዊ በሆነ እንቅስቃሴ ላይ ነው ። አዲሱ ኅብረተሰብ አዲስ ሥርዓት ሁልጊዜ አሮጌውን ኅብረተሰብና አሮጌውን ሥርዓት እየሻረውና እየተካው ይሄዳል ። አንዱ አዲስ ሥርዓት አሮጌውን ሥርዓት በሚተካበት ጊዜ አድኃሪ ኃይሎች የዱሮውን የወደቀውን ሥርዓት በናፍቆት እየተመለከቱ «ዱሮ ቀረ እንጂ ዛሬ ምን አለና» ይላሉ ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የኅብረተሰብም እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ወደፊትና ወደተሻለ ስለሆነ አንድ አዲስ ሥርዓት አሮጌውን ሥርዓት በሚተካበት ጊዜ ፤

አዲሱ ሥርዓት ከዚህኛው በፍጹም አቅጣጫ የተሻለ ይሆናል ።

ይህም ማለት አዲሱ ሥርዓት ከቀድሞው ሥርዓት የሚሻለው የምርት ኃይሎች በመደበላቸው ፤ ዕውቀት በመስፋፋቱና ምርት በማደጉ ብቻ አይደለም ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ከምርት ኃይሎች ማደግና መሻሻል የተነሣ በሰዎች መሐከል ያለው ግንኙነት የተሻለና ከዱሮው ይበልጥ ለሥራና ለዕድገት ያመች ይሆናል ማለት ነው ። በዚህ አንፃር ሲታይ የፊውዳል ሥርዓት ከባርያ አገዛዝ ሥርዓት የተሻለ ነበር ። የካፒታሊስት ሥርዓት ከፊውዳል ሥርዓት የተሻለ ነበር ። የሶሻሊስት ሥርዓት ደግሞ ከካፒታሊስት ሥርዓት የተሻለ እንደሆነ ጥርጥር የለውም ። የሰው ልጅ በትግል ገፍቶ የኮሚኒስት ኅብረተሰብ በሚገነባበት ጊዜ ደግሞ፤ እስከዛሬ ካጋጠሙት ሥርዓት ሁሉ የተሻለ ኅብረተሰብ እንደሚመሠረት ጥርጥር የለውም ።

እንግዲህ የታሪክ አቅጣጫ የኅብረተሰቦች ዕድገት ፋና በአጠቃላይ ወደፊት ነው ማለት ነው ግን እዚህ ላይ በጣም መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። እንደማንኛውም የዲያሌክቲክ የለውጥ ሕግ ይህም በጣም አጠቃላይ ሕግ ነው ። ስለሆነም የታሪክ እርምጃ በአጠቃላይ ወደፊት ነው በሚባልበት ጊዜ ፤ የታሪክን ሒደት በ፻ በመቶ በሺህ ዓመት መልኩ በመመልከት እንጂ በየዕለቱ ፤ በየዓመቱ የሚታየውን ሒደት አይደለም ። ይህ የረዥም ጊዜና አጠቃላይ ርምጃ ሲባል የአንድ ኅብረተሰብ ዕድገት መውደቅ መነሣት ፤ አንድ አብዮታዊ ትግል ከደረሰበት ከፍተኛ ደረጃ የመቀልበስ አደጋ አያጋጥመውም ማለት አይደለም ። በሁለት በሦስት ፤ በአሥር በሐያ ዓመት መልኩ ሲታይ የአንድ አገር ታሪክ ወደኋላና ወደፊት ሊል ፤ ሊወድቅና ሊነሣ ይችላል ።

ስለሆነም በዚህ አጠቃላይ በሆነ የረዥም ጊዜ ሕግ ተዘናግቶ በአጭር ጊዜ አንፃር ሲታይ ፤ የቅልበሳ አደጋ እንዳለ መርሳት አይገባም ። ለዚህ መቸስ በዛሬው ወቅት የሶሻሊስት ኅብረተሰብን መገንባት ከጀመረች በኋላ እንደገና ወደፋሽስታዊ አገዛዝ የገባችውን ቺሊን መጥቀስ ብቻ ይበቃል። ይህንን የታሪክ እርምጃ ሁኔታ በሚቀጥለው ጥናታችን ጠጋ ብለን እንመለከተዋለን ።

---

## ሐቀኛው ታጋይ

ከገጽ ፴፩ የዞረ

ተጨባጭ ዘዴ ቀምሮ
አንድም እያጠቃ
አሊያም ፊቱን እዞሮ . . .
ከፊልና ዘላቂ
የመደብ ትግል አጋሩን
ስውርና ገሃድ
የአብዮት ጉዞ ጠላቱን
በፊናው ለይቶ
መርሀ ፋክራ . . . ሲተልም
እየታገለ ሲያነቃ
ልሳኑ ከተግባር ሲገጥም
ግብታዊ ርእዮት
ወዝ አደሩ ላይ . . . ሳይጠና
እያጋለጠ ሲታገል
ለሳይንሳዊ ንቃት ሕሊና . . . ! !
እነሆ ያኔ ነው
ታጋይ ለሀቅ እሚበቃው ! ! !
. . . . በርቱእ ልሳኑ
ሀቅን ማሳመኑ
በፍላፃ ብዕሩ
እወን ታን ማብሰሩ . . . .
ከአጉል ጀብደኛ
ከሥርዓተ አልበኛ
ከጥገና አጥባቂ
ከሐረግ ነጣቂ
ከግትር ቀኖናዊ
ከክለሳ . . . ዘማዊ
ሳይታክት መዋጋቱ
እያጋለጠ መምታቱ !
ጢፍና መቅረዝ ሆኖ
. . . . ነዶ ሲቃጠል ሲበራ
ቀይ ሰንደቅ ይዞ
የትግሉን ሂደት ሲመራ . . . ! !
ያኔ . . . ያኔ . . . .
እና . . . . ያኔ ብቻ ነው
አድርባይ ሲንጓለል
. . . . ታጋይ ነጥሮ እሚቀረው
ለሀቅ እሚበቃው ! ! !
ሀቀኛ ታጋይ ያቸንፋል ! !

ሰሎሞን ጸጋዬ (ተማሪ) አ/አበባ